05/17/2017

# ያለ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያዊ መሆን አይቻል

ከመኮንን ዘለለው

በኢትዮጵያችን ከሰማንያ በላይ ብሔር ብሔረሰቦች አሉ ተብሎ ይታመናል፣ አገራችን የነዚህ ሁሉ ድምር ውጤት ነች። በዚህች መሬት የተፈጠሩ ብሔር ብሔረሰቦች የራሳቸው ቋንቋ አላቸው፤ ከነዚህ ውስጥ አገርኛ የሆነ ከግእዝ የመነጨ ፊደል ያለው አማርኛ አንዱ ነው። በዚህ ቋንቋ አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ እንደ መገናኛ እና መግባቢያ አድርገው ተጠቅመውበታል። በጊዜው የነበሩ የኢትዮጵያ ነገሥታትም ሆኑ እስካሁን ድረስ ያሉት አስተዳዳሪዎች የመንግሥት የሥራ ቋንቋ አድርገው ለዘመናት ሠርተውበታል። የአማርኛ ቋንቋ፤ ኢትዮጵያዊያን የሚግባቡበት፣ አገር በጠላት ስትወረር አገናኝና አስተባባሪ መሪ ሆኖ ያገለገለ ከአንድነታችን ጋር የተሳሰረ ቋንቋ ነው። ያለ አማርኛ ቋንቋ እንደ አንድ አገር፣ እንደ አንድ ህዝብ ሁነን ታሪክ አይኖረንም ወይም ልንሠራ አንችልም ነበር። ከብዙ በጥቂቱ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ አፄ ዮሐንስ፣ ከአፄ ምኒልክ እስከ ንግሥት ዘውዲቱ፣ ከአፄ ኃይለሥላሴ እስከ ፕረዚደንት መንግሥቱ ከዚያም እስከ ጠ/ሚኒስትር መለስና እርሳቸውን የተኳቸው ጠ/ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ ድረስ፤ከፋም ጠቀመም በነኝህ ስርአቶች ስር ሁነን ታሪክ እየሠራን ያለነው በአማርኛ ቋንቋ አገልግሎት እንደሆነ ታሪክ ራሱ ምስክር ነው። አገራችን ኢትዮጵያን ከማንም ጠላት ለመከላከል ወላጆቻችን ባማርኛ ቋንቋ ተግባብተው ሦስት ቀለማት ሰንደቅ አላማችንን በማውለብለብ፤ ተርበው፣ ተጠምተው፣ ደክመውና ቆስለው፣ ሞተውና ደማቸውን አፍስሰው፣ ነፃነታችንን ጠብቀው አኩሪ ታሪክ እንዳስረከቡን ሁላችን የምናውቀው ነው።

አማርኛ ቋንቋ ጠላት ሲመጣ ብቻ የሚያሰባስበን ሳይሆን በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊ፣ በባህልና ወዘተ… አገራችን እንደ አገር እንድታድግ የበኩሉን አስተዋፅኦ ያደረገ ቋንቋ ነው። ስለዚህ ኢትዮጵያና አማርኛ ቋንቋ፣ ሦስቱ ቀለማት አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ሰንደቅ ዓላማችን ባንድ ላይ፣ አንድም ሦስትም ናቸው። ሦስቱ ለኛ ለኢትዮጵያዊያን የማይለያዩ የማንነታችን ምልክትና፣ የታሪካችን አርማዎችና የአንድነታችን ምሰሶዎች ናቸው። ይሁን እንጂ በሰንድቅ ዓላማችን ላይ የሚቀመጠው መንግሥታዊ ዓርማ ህዝቡ የተቀበለውና የመከረበት ቀጣይነት ያለው ቢሆን በየጊዜው ለሚነሱት ውዝግቦች መፍትሔ ለመስጠት በታቻለ ነበር። ለዚህ መንስኤው በተለያዩ ስርአቶች ውስጥ እየፀደቁ የሚወጡ ሕገ መንግሥቶች ከመነሻቸው ህዝባዊ ተሳትፎንና ይሁንታን በሐቅ ያልያዙ በመሆናቸው እንደ መንግሥታቱ ያገልግሎት ዘመናቸው አጭር ነው። አንድ ብሔራዊ ቋንቋ አማርኛ በቀጣይነት ብንጠቀምበት እንደ አንድ አገርና ህዝብ ለረዥም ዘመን የተጠቀምንበት ስለሆነ ለምን እንዲዳከም ይደረጋል? በምንስ ፍላጎት? በህዝብ ወይስ በመንግሥት። ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ይሁን ከዓለም ረጅም ታሪክ ያላት ፊደሏ ከእንግሊዝኛ፣ ፈረንሳይኛ እና አረብኛ፣ የማያንስ ሆኖ እያለ ለምን በፖለቲካ መሰሪነት ይህ ጥንታዊና አገራችን እዚህ ያደረሰ ቋንቋ እንዲቀጭጭ ለምን ይደረጋል? በዚህ ተግባር ተጠቃሚስ ማን ነው? በኔ ዕይታ ይህ ዕኩይ መንፈስ በህዝቡ ተሳትፎ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲቆም መደረግ አለበት ። በኢትዮጵያ ምድር የበቀሉ ብዙ ብሔር ብሔረሰቦች እንዳሉ ከላይ ለመግለፅ ሞክሬ ነበር፣ እነርሱም በጥቂቱ ለመዘርዘር

ያህል፤ አማራ፣ ትግራይ፣ ኦሮሞ፣ አፋር፣ ሱማሌ፣ ከምባታ፣ ጉራጌ፣ጋምቤላ፣ወላይታ ወዘተ… ተብለው የሚጠሩ አሉ። የራሳቸውም ቋንቋ እንደስማቸው አላቸው። የእያንዳንዱ ብሔር ብሔረሰቦች ቋንቋ ማደግና መበልጸግ አለበት ብየ አምናለሁ። ቋንቋ ጥሩ የመገናኛ መሳሪያ ነው፣ ሁሉም ሰው የግድ አማርኛን ሊያውቅ ስለማይችል አፉን በፈታበት ቋንቋ ቢናገርና ሥራውን ቢያካሂድ ለቅልጥፍና አመቺ ይሆናል። ከሌሎች ቋንቋዎች ለይቼ አማርኛ የኢትዮጵያውያን ቋንቋ ነው ስል፣ ሌሎቹስ እንዲያውም አማርኛ  እኮ ሌሎች ቋንቋዎች በመደፍጠጥም በመዋጥም በማፈንም ያደገ ቋንቋ ነው ከኛው በምን ይበልጣል በማለት ሌላም ሌላም ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። መብትም ትክክልም ነው። ሐቁ ለመናገር  በኢትዮጵያ ምድር የበቀሉት ሁሉ ቋንቋዎች የኢትዮጵያውያን ሐብት ናቸው፣አንዱም ካንዱ አይበላለጥም። ይሁን እንጂ ሌላውን ተወት አድርገን ሐቁን እንናገር  ከተባለ የአማርኛ ቋንቋን ያህል ሁሉንም የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች በስፋት ተግባብተው የተጠቀሙበት የጋራ ቋንቋ ካማርኛ በቀር ሌላ ቋንቋ አልነበረም፣ የለምም።

እኛ ኢትዮጵያዊያን እንደ አንድ አገር፣ እንደ አንድ ህዝብ ሁነን በመተባበርና በመደማመጥ ታሪክ የሠራንበት ቋንቋ አማርኛ  ብቻ ነው፣ በዛሬው አነጋገርም የፌዴራል መንግሥቱ የሥራ እና የአስተዳደር ቋንቋ ሆኖ ለማገልገል የበቃ አማርኛ ብቻ እንደ ሆነ በተግባር ያስመሰከረ ነው። ይህንን ታሪካዊ እውነታ የማይቀበል ኢትዮጵያዊ ያለ አይምስለኝም፣ ከኢትዮጵዊነት ራሱን ያገለለ ካልሆነ በቀር። ለዚህ ነው አማራነት ኢትዮጵያዊነት ነው፣ አማርኛ የኢትዮያዊያን ቋንቋ ነው የምለው። ይህ ቋንቋ ለአማራ ብሔር ብቻ የተሰጠም አይደለም። አገር በቋንቋ ሲከለል ግን የሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች ድምር ቋንቋ መሆኑ ቀርቶ፣ ያንድ ብሔር ቋንቋ ብቻ እንዲሆን እየተገፋ በመሆኑ በጣም ከማሳዘኑ ሌላ  የሚያሳፍርም መስሎ ይሰማኛል።

ህወሐት/ኢህአዴግ መንግሥት የሥልጣን መንበሩን ከተቆጣጠረበት ጊዜ ጀምሮ ነገሩ ሁሉ ተገለባብጧል ብል እውነቱን የሳትኩ አይመስለኝም። ከላይ እንደጠቀስኩት ኢትዮጵያ የዜጎቹዋ ድምር ውጤት ከሆነች፣ በኢትዮጵያ ምድር የበቀሉት  ብሔረሰቦች ማለትም በኢህአዴግ የዘመኑ አጠራር፣ የብሄርና ብሄረሰቦች የሚል ስም ተሰጥቷቸው፣ በየቋንቋቸው የክልል አጥር በማበጀት፣ የብሄር ብሄረሰቦች መንግሥታትና አገሮች እንዲሆኑ፣ ክልሎች የራሳቸውን ቋንቋ እንዲጠቀሙ፣ አማርኛ ፣ እንደ አንድ አገርና ህዝብ፣ አስተሳስሮን የቆየውን ቋንቋ እንዲዳከም በማድረግ ኢትዮጵያን ለመበታተንና ህዝቧንም ከፋፍለው ለመግዛት የሚጠቀሙበት ስልት ይመስለኛል። የጋራ የሆነውን ቋንቋ የበለጠ ማሳደግ ሲገባ፣ የየክልሎቹን ቋንቋዎች ብቻ ነጥሎ እንዲያድግ መደረጉን ስንመለከት፣ የስርዓቱን አደገኛ አካሄድ የሚያመላክት ነው። እኔ የብሔር ብሔረሰብ ቋንቋ እና ባህላቸው እንዲጠበቅ እንጂ የምቃወም ሰው አይደለሁም ቋንቋቸው በጣም አድጎ ሁሉም ብሔር ብሔረሰብ እንደ አማርኛ የሚጠቀምበት ደረጃ ቢደርስ ደስታየ ነው። የሚጠቀም እንጂ የሚጎዳ ኢትዮጵያዊ የለም፤ አይኖርምም። እኔ እየተቃወምኩ ያለሁት የሁሉም ቋንቋ የሆነ አማርኛ ለምን እንዲዳከም ይደረጋል ነው?

ህወሓት/ኢህኣዴግ የሠራው ጥሩ ነገር የለም ብሎ ለማለት እንኳን ባንደፍርም፣ ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ያገራችንን ህልውና የሚያጠፉ፣ ጨርሶ የሚበታትን ድርጊት እየሠራ እንደሆነ ግልፅ ነው። ይህ እቅድ የፋሽስት ኢጣልያ አገራችንን በወረረበት ዘመን ህዝባችንን በቋንቋ ከፋፍሎ አገራችንን ሊበታትን ጀምሮት ግን ሳይሳካለት የቀረ

ሴራ እንደነበረ ታሪካችን ያስረዳል። አሁን በሥልጣን ያለው ስርዓት፣ ዛሬ ጠላቶቻችን እኛን ለመከፋፈል የተጠቀሙበት ዘዴ ለማስፈፀም ሽር ጉድ ሲል ስንመለከት፣ ሁላችንም ኢትዮጵያዊያን ይህ መንግሥት ኢትዮጵያዊ ነው ወይስ የጠላቶቻችን ስውር ዓላማ ለማስፈፀም የቆመ ጠላት የሚል ሐሳብ በአዕምሯችን መቀረፁ አይቀርም።

ስለዚህ ህወሓት/ኢህአዴግ ማን ነው? ለምንስ እንዲህ ያደርጋል? እንዴትስ ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና ጥቅም ለመቆም ሞራል ያጣል? ዛሬ ኢትዮጵያዊነት በክልል ተከፋፍሎ ተዳክሟል፣ የኢትዮጵያዊያን የጋራ ቋንቋ አማርኛን ተተኪው ትውልድ እንዳይጠቀምበትና እንዳይስፋፋ፣ በየክልሉ ቋንቋ ላይ ብቻ እንዲያተኩር በመደረጉ እየተዳከመ መጥቷል። ይህንን ችግር ለማስወገድ ጥረት በማድረግ ፈንታ፣ አሁን የሚታየው የኢትዮጵያ ህዝብ ተዳክሞና ተበታትኖ ማጉረምረም ብቻ ሆኖ ነው የሚታየው። ስርዓቱ ግን በአንፃሩ፣ ኢትዮጵያ አንድነትዋ የተጠበቀው እኔ ስላለሁኝ ነው፣ እኔ ከሌለሁ አገሪትዋ ትበተናለች እያለ በማስፈራራት፣ የመበተንና የማዳከም ሥራውን በስውርም ሆነ በይፋ ቀጥሎበታል።

ኢትዮጵያ አንድ ናት፣ በኢትዮጵያ ያለው አንድ ህዝብ ነው፣ አንድነት ኢትዮጵያዊነት ብቻ ነው፣ አንድ ህዝብ አንድ አገር አንድ ሰንደቅ ዓላማ  አንድ የጋራ ቋንቋ ለሁላችን የሚያግባባ አለን። በጎደለው ሞልተን አብረን ለመኖር የሚያስችሉን እሴቶች በርካታዎች ናቸው። እኛ የምንመኘው ፍትህ፣ ዴሞክራሲና እኩልነት በመቻቻልና በመከባበር፣ የተለያዩ የብሔር ብሔረሰቦች ቋንቋዎቻችንንም አበልፅገን በሰላም መኖር ነው፣ የምንፈልገውም ይህንን ብቻ ነው። አትለያዩን የሚል አስተሳሰብና አነጋገር በህወሓት/ኢህአዴግ መሪዎችና ተከታዮች ሲመነዘር፣ የኋላ ቀር አስተሳሰብ፣ የነፍጠኞችና የደንቆሮዎች አነጋገር፣ የስልጣን ናፋቂዎች አስተሳሰብ ነው በማለት፣ ያለ የሌለ ኃይሉን ተጠቅሞ ያፍናል፣ ያስራል፣ ይቀጣል፣ ይገድላልም።

በማጠቃለል የምዕራባዊያን ጠላቶቻችን ኢትዮጵያን የመበታተን ዕቅዳቸውን በሰሜን ያገራችን ግዛት ቀይ ባሕር በኩል ወደ ኤርትራ በማስገባት፣ እነ ኢሳያስ አፈወርቅን በማሰማራት፣ ዙሪያ መለስ  ዕገዛ በማድረግ ኤርትራን እንድናጣ እንዳደረጉ የትናንት ታሪካችን መሆኑን እናውቃለን ። በሶማሌና ኦሮሞ ህዝብ ወንድሞቻችንም በኩል ኢትዮጵያን የመበታተን ዕቅዳቸውን በማስፋፋት፣ ነፃ አውጪ የሚል ድርጅት አቋቁመው በጠላቶቻችን እየተደገፉ በመንቀሳቀስ ብዙ ዘመን የብተና ሥራ እንደተሠራ ሁላችንም የምንገነዘበው ሐቅ ነው።

በመቀጠል በትግራይ በኩል ደግሞ የህወሓት መሪዎች የምዕራባዊያንና የኤርትራ ነፃ አውጪ መሪዎችን ተልዕኮ በመቀበል፣ ለብሄረ ትግራይ ተቆርቋሪ መስሎ በመቅረብ የህዝብ ድጋፍን ካገኘ በኋላ፣ ስትራተጂ ዓላማውን በመካድ፣ ማለትም የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና እኩልነትን በመካድ፣ የትግራይን ህዝብ በማታለል ከዚያም ቀጥሎ ጠቅላላ የኢትዮጵያ ህዝብን በማታለል፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ዴሞክራሲታዊ ግንባር (ኢህአዴግ) የሚባል ድርጅት በማቋቋም፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኢህዴን) (EPDM) በማሽመድመድ እንደነ ኢህአፓ ሌሎቹም የአንድነት ፓርቲ የሆኑ ሁሉ በማጥፋትና በማግለል ኢትዮጵያን የመበታተን ደባውን የምዕራባዊያን ጠላቶቻችን ዕቅድ በስመ ኢትዮጵያ ለማስፈፀም ሌት ከቀን እየሠራ ይገኛል።

ከላይ በተገለፀው መሠረት አገራችን እየተዳከመችና የመበታተን አዝማሚያ እየታየባት ነው፣ አንድነታችንም እየተናደ ይገኛል። እኛ ኢትዮጵያዊያን ምን ማድረግ ነው የሚጠበቅብን?

ይህንን ጥያቄ ከመመለሳችን በፊት አገሪትዋን በመምራት ያሉ ህወሐት/ኢህአዴግ ምን ይመስላሉ? ምንስ እያሉን ነው? ራእያቸው ምንድን ነው? የሚናገሩትና የሚሠሩት ካገሪትዋ ጥቅምና ከህዝቧ ሕልውና ጋር ይጣጣማል ወይ? የሚለውን ማወቅ ለጥያቄው መልስ ግማሽ መንገድ ነው ብየ አምናለሁ።

የህወሐት/ኢህአዴግ ቀንደኛ መስራቾችና መሪዎች ከሚባሉት በጥቂቱ የተናገሩትን እንመልከት፦

የኢትዮጵያ ጠ/ምኒስቴር የነበሩት አቶ መለስ ዜናዊ "የአክሱም ሐውልት ለወላይታ ምኑ ነው!?" ብለው ነበር። አቶ ስብሐት "የአክሱም ታሪክ ተምቤንና አጋሜን የሚጨምር አይመስለኝም" በማለት በአንድ መድረክ መናገሩ ተመዝግቦ ያለፈ ታሪክ እንደሆነ እናውቃለን።

አቶ በረከት ስምዖን በሰበሰበው የኑ እንወያይ መድረክ የመንግሥት ደጋፊዎችና ተቃዋሚዎች እነ ዶክተር መራራና እንጅነር ይልቃል በተገኙበት አቶ ስብሐት ነጋ "ኢህአዴግ ኢትዮጵያን 50/% አያውቃትም ኢህአዴግ ራሱን ማጥፋት አለበት ራሱ እንደሚያጠፋ ያውቃል" ብሎ ሲናገር ህዝብ አዳምጧል።

በሌላ ጊዜ ደግሞ አቶ ስብሐት ነጋ "አንድ አገር፣ አንድ ቋንቋ፣ አንድ ሐይማኖት እያሉ ተረት ተረት የሚያወሩና ዕንቅፋት የሆኑትና ይህንን ሥራ በመሪነት የያዙት የአማራና የኦርቶዶክስ ሐይማኖት ተቋም ነበር፣ እርሱንም ራሱን መትተነዋል" በማለት በመናገሩ ብዙ ኢትዮጵያዊያንን እንዳሳዘነ ይታወሳል።

በቅርብ ጊዜም አቶ ስብሐት በአዲስ አበባ ሚሚ ስብሐቱ የተባለች ጋዜጠኛና የዛሚ ሬድዮ ባለቤት "ተሐድሶ እስከ መቼ" በሚል ርዕስ ሥር ለውይይትና ጥያቄና መልስ ቀርቦ ሃሳቡን ገልጾ ነበር። ከተጠየቀው ጥያቄዎች ለአንዱ መልስ ሲሰጥ እንዲህ ብሎ ነበር "እንደ ኢህአዴግ ለህዝቡ የሚያስብ የለም፣ በኔ ጊዜ ህዝብ የሚፈልገው ሰላም፣ የኢኮኖሚ ዕድገትና አንድነትን እያገኘ ነው" ይለናል። ጠያቂዎቹ "ካሁን በፊት የነበሩት ገዢዎችም እኮ እንደዚያ ነበር የሚሉት፣ እስካሁን ግን ህዝቡን ችግርህ ምንድነው ብሎ የሚጠይቀው አግኝቶ አያውቅም"። "ኢህአዴግ ጥልቅ ተሐድሶ እያደረግኩኝ ነው ይላል፣ ነገር ግን ራሱ የችግሩ አካል ሲሆን እንጂ ችግር ሲፈታ አይታይም፣ እርስዎ ምን ይላሉ? አቶ ስብሐት "የኢትዮጵያ ህዝብ እንግዳ ተቀባይ ህዝብ ነው ይባላል፣ ግን እንደ ኢትዮጵያ ህዝብ እንግዳ የሚጠላ የለም፣ እንግዳ ሲመጣበት የሚሸሽግ ህዝብነው፣ በበሽታና በጥይት እየሞተ፣ ታታሪ ህዝብ ነው ይባላል፣ አገሩን ላለማወቅ ጥረት ይደረጋል፣ አገር እኮ አልነበረንም! አንዱ ግማታም፣ አንዱ ባሪያ እየተባለ የሰው ልጅ እየተሸጠ ነበር፣ እንደሰው የሚቆጠር እኮ አልነበረም። "ህዝቡ እኮ ማዕከላዊ መንግሥቱን እየተዋጋው ነበር የኖረው። ያለፉት መንግሥታት ከሶማሌ፣ ከጣልያን እንደተዋጋ ሁሉ፣ የራሱንም ህዝብ ሲወጋ እኮ ነው የነበረው፣ አገር እኮ አልነበረንም! የተወሰኑ ጦርነት ነበሩ እንደ ዓድዋ ጦርነት፣ መደረግ አልነበረበትም፣ አርበኝነት ጠፋ እና አገር ቆርጠን ሸጥን፣ የማይገባ የዓድዋ

ጦርነት አደረግን፣ አሁን ግን አገራዊነትን ለመመስረት እየጣርን ነው። ጠላቶቻችን ጠባብነትና ትምክህተኝነት ናቸው፤ ኢህአዴግ ሥልጣን ይዞ መቀጠል አለበት፣ ባለቤቶቹ እስኪመጡ ድረስ፣ ኢህአዴግ ለባለቤቶቹ አስረክቦ መጥፋት አለበት። እንግዲህ ባለቤቶቹ ልማታዊ ባለሃብቱና ወዛደሮቹ ናቸው። (የተሰመረበት የራሴ ነው።) ስለዚህ ለውጥ የሚያመጣው ኢህአዴግ ብቻ ነው፣ ኢህአዴግ ጥልቅ ተሐድሶ በማድረግ በድል ይወጣል የሚል እምነት አለኝ ነገር ግን፣ ለውጥ ካላመጣ፣ ኢትዮጵያ ትበተናለች እኛም ተመልሰን ወደ ጥይት እንገባለን፣ በሰላም ደግሞ አንለያይም፣ ኢትዮጵያም ትጠፋለች፣ ትበተናለች" ብሏል።

እንግዲህ የኢህአዴግ ገዢ ፓርቲ መሪዎች ሆኑ አባሎች በተለያየ ወቅት የተናገሩትን ሁሉ ለመዘርዘር ጊዜና ቦታ ስለሌለን ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ያነበበ ግለሰብ የራሱ እይታ ሊኖረው ይችላል በኔ እይታ ንግግሮቹ ምን መልዕክት ለማስተላለፍ እንደፈለጉ ለማቅረብ እሞክራለሁ።በመጀመሪያ የህወሐት/ኢህአዴግ መሪዎች የሚናገሯቸው ሐሳቦች የኢህአዴግ አቋሞች/ራእዮች አይደሉም የሚሉና የሚጠራጠሩ ሰዎች ካሉ የዋሆች ወይም ከህወሐት/ኢህአዴግ የተለየ ራእይ ያላቸውን ሰዎች ለማዘናጋት የሚሞክሩ መሆን አለባቸው።

መሪዎቹና ተከታዮቹ የሚሉት ሁሉ እንዳለ ሆኖ ሊያስተልልፉት የሚፈልጉት ደባ በኔ ዕይታ ሲፈተሽ ይህን ይመስላል፦ ሟቹ አቶ መለሰና በዕድሜ የታደሉት አቦይ ስብሐት ነጋ "የአክሱም ሐውልት ለወላይታ ምኑ ነው?" "የአክሱም ታሪክ ተምቤንና አጋሜ አውራጃ የሚጨምር አይመስለኝም" ሲሉ በጠቅላላ ኢትዮጵያ የምትባል አገር እንደማያውቋት ሊያውቋትም እንደማይፈልጉ በኢትዮጵያ ስም የሚጠራ አገር ሊኖረንም ፍላጎት እንደሌላቸውና በጣም ጠባቦች እንደሆኑ ቁልጭ አድርጎ ያሳያል።

አቶ ስብሐት ከዚህ በላይ ከተናገራቸው ወስደን ስናያቸው የኢህአዴግ ገዢ ፓርቲ አገራችን ኢትዮጵያን በሚመለከት ያለውን አቋም/ራእይ መገንዘብ ይቻላል። አቶ ስብሐት "ኢህአዴግ ገዢ ፓርቲ ኢትዮጵያን ከመቶ ኃምሳውን አያውቃትም" ይለናል አገሪትዋን የማያውቅ ፓርቲ እንዴት የአገሪቱ ዕድል ወሳኝ ሆኖ ተመረጠ፣ እንዴት ለ26 ዓመታት አመራሩን ጨብጦ ሊቆይ ቻለ? አቶ ስብሐት ቀጥሎ "አገር እኮ አልነበረንም" "ግማታም ባሪያ እየተባለ እየተሸጠ ነበረ አንድነት የሌለው አንድ አገር አንድ ህዝብ ይባላል ግን እንደጠላት ሲጨፈጨፍ ነበር" ይላል። ዛሬስ በኢህአዴግ አገዛዝ ጭቆናው እንዳለ ሆኖ በጠራራ ፀሐይ ዓለም እስኪገረም በጥይት በጅምላ እየተገደለ ያለው በዕስር ቤት ውስጥ ታጉሮ እየተደበደበ ለመገደል የሚጠባበቅ ህዝብ ማን ሆነና ነው አቶ ስብሐት ባለፉት ገዢዎች ላይ ክሱን የሚደረድረው። ምንም ሳያፍር በኔ ጊዜ ህዝቡ ሰላምና የኢኮኖሚ ዕድገት እያገኘ ነው፣ ኢህአዴግ ለህዝብ የሚያስብ ድርጅት ነው ማለቱ በዚህ ዕድሜው ያሳዝናል። የሚገርመው በዓለም ውስጥ ጨቋኝና ተጨቋኝ አለ የጭቆናው ዓይነት ግን ይለያያል ህዝብ ስለተጨቆነ አገር የለውም አይባልም፣ አገርማ ነበረው አሁንም አለው እንዲያውም ከሚያስደንቅ የአባቶቻችንና እናቶቻችን ጀግንነት ታሪክ ጋር ነው። አቶ ስብሐት የሚያዳምጠው የለም እንጂ አገር እያለን አገርና ታሪክ የሌለን ህዝብ እንድንሆን እየነገረን ነው፣ አሁንም የሚገርመው ኢህአዴጎች አገር የለም እያሉ፣ አልነበረንም እናውቀውም እያሉ የማያውቁትን አገር መግዛታቸውን ነው። አቶ ስብሐት ይህ አንድነት የሌለው ያለውን ህዝብ በአፄ ምንሊክ መሪነት ባንድነት ሆኖ የሰራው የአድዋ ድል ታሪክ ለተገናገረውን ሁሉ

ስለሚያፈርስበት እንዲህ ይላል “በአድዋ ጦርነት ተደርጎ ትልቅ ስራ ተሰርቷል ይሁን እንጂ ጦርነቱ ሊደረግ አይገባውም ነበር አርበኝነት ጠፋ እና አገር ቆርጠን ሸጥን ወደ ጦርነት ገባን” ይላል። አሁንም የኢትዮጵያ አንድነት ጀግንነትና አገር ወዳድነት ታሪክ ላለመቀበል ኤርትራ በጣልያን ስር በመቆየትዋ ወደ ጦርነት ገባን በማለት ዓለም ያደነቀውን የጥቁር ሰው ታሪክ ሊያዳፍነው ይሞክራል። በጣም የሚገርመው በቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ዘመን ኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ በመመለስ በድል የተገባደደውን ታሪክ እያለን ትንሽ አለማፈሩ ትናንትና እሱና ጓደኞቹ የውርደት መዝገብ ተሸክመው ወደ ተባበሩት የዓለም ምንግሥታት መስሪያ ቤት ኒው ዮርክ በመሔድ ጀግኖች ወላጆቻችን ያስተካከሉትን ታሪክ ማፍረሳቸው ማፈር ሲገባቸው እነሱ ጀግኖች ሌላው ህዝብ ጀግንነት እንደ ሌለው አድርጎ ለማቅረብ መሞከር ለምን አስፈለገ? ብዬ ሳስብ ይቅርታ ይደረግልኝና የባንዳዎች አባቱ አጎቶቹና አያቶቹን ሒሳብ እያወራረደ መሆኑ ገባኝ። “የሚሉሽን ብትሰሚ ገቢያ ባልወጣሽ” ብለን ብናልፈው ይሻላል። እኔ ኤርትራዊያን ኢትዮጵያዊያን መሆን አንፈልግም ካሉ ተገንጥሎ መኖር መብታቸው ነው እየኖሩም ነው። ለኢትዮጵያ ጥቅም አለመቆም ግን ህወሐት/ኢህአዴግ ከተጠያቂነት አያመልጥም እያልኩኝ ነው፣ይታወቅልኝ።

አቶ ስብሐት በመቀጠልም “የኢትዮጵያ ህዝብ ዕንግዳ ተቀባይ ህዝብ ነው ይባላል ግን እንደ ኢትዮጵያ ዕንግዳ የሚጠላ የለም ዕንግዳ ሲመጣበት የሚሸሽግ ህዝብ ነው” ይላል። ራሱ ተናጋሪውን በጣም የሚያስገምት አነጋገር ነው። አቶ ስብሐት ከትግራይ ተወልዶ ያደገ በትግል ጊዜም የትግራይ ገበሬ እያዋጣ እንጀራ፣ ዳቦ ሆነ ቆሎ የሰጡት እየበላ የታገለና ያታገለ ሰው፣ እስካሁን ደህና ቦታ ያለው በህዝቡ ሩህሩህነት፣ ለጋስነትና ዕንግዳ ተቀባይነት ካለችው ትንሽዋን ለራሱ ትቶ ብዙውን የሚሰጥ ህዝብ ማህል የተንቀሳቀሰና ባይኑ ያየ ሰው እንዲህ ብሎ መናገሩ በተለይ ለኔ እና ለሚያውቁት ሰዎች እጅግ በጣም የሚያሳዝን አነጋገር ይመስለኛል። ሌላው ይቅርና እሱ ራሱ በሚኖርበት አዲስ አበባ ከተማ ህዝብ በህወሐት መጥፎ አስተዳደር ቤቱን ትቶ የተሰደደውን የትግራይ ለማኝ የተሸከመውን ህዝብ አይቶ እንኳን የኢትዮጵያ ህዝብ ምን ያህል ለዕንግዳ ይሁን ለተቸገረ በጣም ለጋስና ትሁት መሆኑን ብቻ መረዳት ከባድ አይደለም። ኢትዮጵያ አገራችን በዓለም  የምትታወቀው በዕንግዳ ተቀባይነትዋ መሆኑ እየታወቀ እንዲህ ብሎ መናገሩ፣የኢትዮጵያ ህዝብ ባህሉን ታሪኩን ማጥላላት ስለፈለገ ብቻ ይመስለኛል። ሌላው ጉዳይ ኢህአዴግ ኢትዮጵያን አያውቃትም ላለው አነጋገር እውነትነቱን ያረጋግጣል። አቶ ስብሐት “አንድ አገር አንድ ህዝብ አንድ ቋንቋና አንድ ኃይማኖት እያሉ ተረት ተረት የሚያወሩና ይህንን ሥራ በመሪነት የያዙት የአማራና የኦርቶዶክስ ኃይማኖት ተቋም ናቸው እነሱ መተናቸዋል” ይላል። አዎ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ኃይማኖት ካርባ ሚሊዮን በላይ ህዝብ ያሰባሰበ ተቋም እንደ ሆነ፣ ይህ ተቋም ደግሞ ኢትዮጵያ የምትባል አገር እንድትኖረንና ለህልውናዋ ምክንያት ከሆኑ ሌሎች ተቋሞች አንዱ ነው። ሌላው በሚሊዮኖች የሚቆጠር የኢትዮጵያ ህዝብ ያሰባሰበ የዕስልምና ኃይማኖት ተቋምንና ሌሎችንም መጥቀስ ይቻላል። የነዚህ ተቋማት በኢትዮጵያ ህልውና ትልቅ ስፍራዎች እንዳሏቸው ይታወቃል። ህወሐት/ኢህአዴግ ይህንን ያውቃል፣ በድርጅት ኃይል የት እንደደረሰም ጠንቅቆ እንደሚያውቅ እንገነዘባለን። ስለዚህ በኃይማኖት ይሁን በሌላ ምክንያት የተደራጀ ኃይል ያስፈራዋል፣ በዛም ላይ ህወሐት/ኢህአዴግ አገር አልነበረንም ኢትዮጵያን የሚያውቃት የለም ሲል ኢህአዴግ እሱ የሚያውቃት አገርነት

ለመፍጠርም እንደሚጥር ገልጧል። ኢትዮጵያ እንዳልሆነች ግን ጥርጥር የለንም። እነሱ የሚፈልጓት ለሎዓላዊነትዋ የሚቆሙላት አገር ማንና ምን እንደምትመስል አናውቅም። ስለዚህ የህወሐት/ኢህአዴግ አቋም/ራእይ የማይከተል ማናቸውም ተቋም እንዲከስም ይደረጋል፣ ካልሆነ እንዲበተንና እርስ በራሱ ሳይስማማ እንዲከፋፈል ይደረጋል። ከዚያም እስከ መታሰርና መገደልም ሊኖር እንደሚችል እያየን ነው። የህወሐት መሪዎች በትግራይ ውስጥ በድርጅትና በተቋሞች ላይ የፈፀሙት ከዚህ የተለየ አልነበረም። ተቋሞች ይህንን ስርዓት ካልታገሉት የሚጠብቃቸው አቶ ስብሐት ያሉትን እንደ ሆነ ሊጤን ይገበዋል።

አማራው ለምንድን ነው የተተኮረበት? ህወሐት/ኢህአዴግ አማራ ሲል አማራው ብሔር ብቻ አይመስለኝም ሌላው ትልቁ የነ ስብሐት ትኩረት ግን አማርኛ ተናጋሪው ኢትዮጵያዊ ህዝብ መበታተንና ማዳከም ነው። አማርኛ ተናጋሪ የአማራ ብሔር ብቻ አይደለም፣ የአፉ መክፈቻ አማርኛ የሆነ ስንት ጉራጌ፣ ዓፋር፣ ጋምቤላ፣ ትግራይ፣ ወላይታ፣ ኦሮሞና ሌሎችም በጣም ብዙ ህዝብ ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ ያደረገ አማርኛ ተናጋሪ አለ። ይህንን ለመበተን ነው የሚታገለው። ምክንያቱም ይህ አማርኛን ቋንቋው አድርጎ ታሪክ እየሠራ የመጣ ኢትዮጵያዊ ሁሉ መበተን አገር ከማፍረስ አይተናነስም። እባካችሁ ከክልል በላይ እናስብ፣ ክልል እኮ ቋንቋን መሰረት ያደረገ ኢትዮጵያዊያን ከልልሎ ለያይቶ የመበተን የህወሐት/ኢህአዴግ ዘዴ/ስልት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን ባቢሎን ግምብ የፈረሰው መግባብያ ቋንቋ ሲጠፋ ነበር። ስለዚህ ጠቅለል አድርጌ ሳየው ክልል የሚባል ያመጡልን እነሱ እንደሚሉት አንድነትና እኩልነት ሳይሆን ለያይተው ለመግዛት የፈጠሩት ማታለያ ነው ። ስለዚህ የሰውን ልጅ ክብር በማያምኑና እንደሰው ሳይሆን እንደ ዕንስሳ በሚመለከቱን ሰዎች በእነ ስበሐት ፖሊሲ ወይም ራእይ እየተመራን መቀጠላችን መቆም አለበት። ያለፈው ይበቃል።

አቶ ስብሐት ነጋ በመቀጠል "ጠላቶቻችን ጠባብነትና ትምክህተኝነት ናቸው፣ ኢህአዴግ ስልጣን ይዞ መቀጠል አለበት፣ ለውጥ የሚያመጣው ኢህአዴግ ብቻ ነው፣ ኢህአዴግ ጥልቅ ተሐድሶ በማድረግ በድል ይወጣል የሚል ዕምነት አለኝ። ለውጥ ካላመጣ ኢትዮጵያ ትበተናለች፣ እኛም ተመልሰን ወደ ጥይት እንገባለን በሰላም ደግሞ አንለያይም ኢትዮጵያም ትጠፋለች ትበተናለች" ብሏል። በጣም በሚገርም ሃለፊነት በጎደለው ዕርስ በርሱ በሚጣረስ አነጋገር ህወሐት/ኢህአዴግ ብቻ ስልጣኑን ይዞ መቀጠል አለበት ሌላው ህዝብም ስልጣን መያዝ እንደሌለበትና ላገሪትዋ ያላት ምርጫ በህወሐት/ኢህአዴግ ገዢ ፓርቲ መመራት ብቻ እንደሆነ ህወሐት/ኢህአዴግ እንደ ድርጅት በጠባብነት እና በትምክህተኝነት ተሸብቦ እናውቅላችሁ አለን በሚል አስተሳሰብ የተሞላ ገዢ ፓርቲ ነው። ከዚህ የበለጠ ትምክህት እና ጠባብነት ምን ሊሆን ይችላል? በተጨማሪ ጠባብነትና ትምክህተኝነት ጠላት እንደሆኑ ሊነግረን መሞከሩ በኔ እይታ ራሳቸው በቅድሚያ መጥፋት እንዳለባቸው እየመሰከሩ ይመስለኛል። ምክንያቱም ትምክህትና ጠባብነት ከጠፋ ህወሐት/ኢህአዴግ ይጠፋልና አይኖርም። በጣም የሚያሳዝነው አስተሳሰብ ደግሞ ኢህአዴግ ጥልቅ ተሐድሶ አድርጎ ማሸነፍ አለበት። ከዚያ በኋላ ለባለቤቱ ለልማታዊ ባለሐብቱና ለወዝአደሩ አስረክቦ ኢህአዴግ መክሰም አለበት ሲል እነሱና ተባባሪዎቻቸው በሰበሰቡት ገንዘብ የሐብታሞች ወይም የብርዥዋ ፓርቲ መስርተው እንደሰሜን ኮሪያ ለአርባና አምሳ ዓመት በስልጣን ለመኖር ነው ህልማቸው። አዎ እንዳሉት በተሐድሶ ስም ልማት

እየተባለ ብዙ ሐብት ተሰብስቧል የቀረው የነሱ የሐብታሞች ማለት የመድብለ ፓርቲ አሰራርና የዴሞክራሲ የፍትሕ ሽታ የሌለው አምባገነን ፓርቲ መስርተው መቀጠል ነው። ህወሐት ኢህአዴግ በዚህ መንገድ ሂዶ ካላሸነፈ ወደ ጥይት እንገባለን፣ በሰላም ደግሞ አንለያይም ኢትዮጵያ ትበተናለች ትጠፋለች በማለት በድፍረት ነግረውናል። ለአቶ ስብሐት ኢትዮጵያ ስትጠፋ እሱ አይጠፋም? ለመሆኑ የት ሊኖር አስቦ ነው? ዕውነቱን ነው አገሬ ቢላት ኑሮ ኢህአዴግ በስልጣን ካልኖረ ኢትዮጵያ እንድትጠፋ አይመኝላትም ነበር። የአቶ ስብሐት ትልቁ ስህተት እሱ ሆነ ኢህአዴጎች ባያውቋትም አገራችን ባይኗትም፣ ይህች አገር አገሬ የሚላት ብዙ ትልቅ ህዝብ እንዳላት እስካሁን አልተገነዘቡም ወይም የህዝብ ንቀት ይመስለኛል። በህወሐት ኢህአዴግ ራእይ ተበታትነናል ተዳክመናል አገር የሌለው ህዝብ ሆነናል። እንግዲህ የኛ ምርጫ ምንድ ነው? እንደ ግመል ጉልበታችን እየተደበደብን መንዝና መመራት ወይም ተባብረን ተከባብረን ተደማምጠን ታግለን ማንነታችንን ማሳወቅ፣ መብታችንና ያገራችን ህልውና ማረጋገጥ፣ አገራችንን ኢትዮጵያ ከህወሐት/ኢህአዴግ በተሻለና በበለጠ አስተዳደር እንድትመራ ማድረግ ጊዜ የማይሰጥ ጉዳይ ይመስለኛል።

የስብሓትን አነጋገር በሚመለከት የተለያዩ አስተያየቶች ሊኖረን ቢችልም፣ ባጠቃላይ ሲገመገምና እስካሁን ድረስ ድርጅቱ ህወሓትና ኢህአዴግ እያከናወናቸው ከመጣ ተግባሮች ስንነዘብ ከላይ ከጠቀስኳቸው በተጨማሪ ጠቅለል አድርጌ ሳየው በሚከተሉት ነጥቦች ሊጠቃለሉ የሚችሉ ይመስለኛል።

፩. ኢትዮጵያን በክልል መሸንሸኑና አንቀጽ ፴፱ን ዋና እና የማይናወጥ መሠረት አድርጎ መቂጠር፤

፪. በኢትዮጵያ ዋና ዋና ጥቅሞች ላይ በሚያደርጋቸው ውሎች ላይ ደንታ ቢስነቱ፤ ለምሳሌ ከኤርትራ ጋር የተደረገው ሪፈረንደም የኢትዮጵያ ህዝብን ፍላጎት ያላካተተ ብቻም ሳይሆን፣ ገና እንደ መንግሥት በህዝብ ተመርጦ አመኔታ ባላገኘበት ሁኔታ መፈጸሙ፣ ቆይቶም እስከ የተባበሩት መንግሥታት ድረስ በመሄድ ኢትዮጵያ የባህር በር ችግር የለባትም ብሎ ያለ የባህር በር ማስቀረቱ፤ በባድመ ጦርነትም በተገኘው ዕድል ጉዳዩን ለተባበሩት መንግሥታት አቅርቦ ለመደራደር የነበረውን ተስፋ በማምከን ስለ ኢትዮጵያ ምንም ግንዛቤ በሌላቸው የውጭ አገር ጠበቆች ተወክሎ ጥቅሞቻችን አለመጠየቅና፣ የቀረቡትም ለኢትዮጵያ የማይጠቅሙ ያረጁና ያፈጁ የቅኝ ግዛት ውሎችን ይዞ በመቅረብ አገራችንን ለዳግም ጥቃት የተዳረገበት ሁኔታ፤

፫. ከሱዳን መንግሥት ጋር የሚያደርገው የውስጥ ለውስጥ ንግግርና በሰሜን ምዕራቡ ያገራችን ክፍል ያለውን ድንበር ፓርላማው ሳያውቀውና ሳይነጋገርበት አሳልፎ ለመስጠት የሚደረገው ደባና ተንኮል፤

፬. ኢትዮጵያ የበርካታ የሰው ልጅ ዘሮች መገኛ እንደመሆኗ መጠን ብዙ ቋንቋ የሚናገሩ ወገኖች ይኖሩባታል። ታዲያ ይህ ብዛታችንና ልዩነታችን እንደ መልካም ጸጋ በመቁጠር ለኅብረተሰቡ የሚስማማ አስተዳደር እንደመፍጠር፣ ቋንቋን መሠረት ያደረገው ያከላለል ሁኔታ ብዙ ችግሮችን እያመጣ ሲሆን ቀመሩ ራሱ ለሁሉም የማይሠራ በመሆኑ፤ ማለትም አከላለሉ ሁሉም በቋንቋ ይሁን ቢባል፣ የደቡብ ህዝቦች የሚባለው ክልል እንኳ እንደምሳሌ ብንወስድ በርካታ ቋንቋ የሚናገሩ ወገኖች የሚገኙበት በመሆኑ ቢያንስ ሃምሳና ስድሳ ክልሎች ይወጡታል ማለት ነው። እስካሁን

ድረስ አብረው ቢኖሩም ኢህአዴግ የክልልን ሥራ እየገፋበት ስለሆነ ችግሩ የሚቆም አይደለም። በተለያዩ ቦታዎች የማንነት ጥያቄ፣ የድንበር ጥያቄ፣ እየተባለ በአፋር፣ በሱማሌ፣ ባማራ፣ በቤንሻንጉል፣ በወልቃይት፣ ወዘተ በየጊዜው ባካባቢው ኅብረተሰብ የሚነሳው ጥያቄና አልፎ አልፎም በመካከላቸው የሚደረገው ግጭት ለሠላም እጦት እየዳረገ መሆኑ ይህንንም ለማስተካከል የሚታየው ዳተኝነት፤

፲. ባለፉት ያገዛዝ ዘመኖች ያማራ ህዝብ ልክ እንደ ሌላው ኢትዮጵያ ህዝብ ሲጨቆን መቆየቱ ግልፅ እየሆነ ለፕሮፖጋንዳ ፍጆታ ተብሎ በህወሓት መሪዎች ይሁን በሌሎች ድርጅቶች በተካሄደበት አሉታዊ ቅስቀሳ፣ ባሁኑ ሰዓት ባማራው ህዝብ ላይ እየደረሰ ያለው በደል ከፍተኛ እና በጣም የሚያሳዝን ነው። በተለያዩ ጊዜያት ለዘመናት ሰፍረውባቸው ከነበሩ አካባቢዎች እንዲፈናቀሉ ሲደረግ፣ በሥልጣን ያለው መንግሥት ይህንን መጥፎ አካሄድ ለመቀልበስና ወደ ትክክለኛው መንገድ እንዲያመራ ለማድረግ የወሰደው እርምጃ አልታየም። በገዛ አገሩ የተፈናቀለውን ወገን ለመርዳት የተደረገው ጥረትም ያን ያህል አልነበረም። የተሰጠው የዜና ሽፋንም ዜሮ ነበር ማለት ይቻላል። ስለዚህ ህዝብ ባገሩ እንደዚህ ሲሆን እያዬ ዝም ያለ መንግሥት ራሱ በድርጊቱ ላይ ተሳታፊ ነው ከማለት ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው መስሎ አይሰማኝም። በመሆኑም ህዝብንና ህዝብን ለማጣላትና የዘር ፍጅት እንዲመጣ እየሠራ በመሆኑ ወደፊት ሊያስከትል የሚችለውን መዘዝና አደገኛ አካሄዱ ምን እያደረገ እንዳለ አመላካች ነው ብዬ እገምታለሁ።

እላይ በዘረዘርኳቸውና ሌሎች እዚህ ልዘረዝራቸው ያልቻልኳቸውንና ሁላችንም የምናውቃቸው ምክንያቶች በመነሳት የህወሐት ኢህአዴግ ድርጅት አመራሮች በህዝቡ ዘንድ ጠብና ጥርጣሬ በማስፈን እርስ በርሱ እያጋጩ ህልውናቸውን ማስቀጠል ነው። ይህ አጀንዳቸው እስከሠራላቸው ድረስ እና የኢትዮጵያ ህዝብ ካደረበት የአንድነትና የመደማመጥ ችግር ወጥቶ ራሱን ማየት ጀምሮ እነርሱን በህዝብ ኃይል መለወጥ እስኪችል ድረስ፣ ባለ በሌለ ኃይላቸው በኢኮኖሚውም፣ ወታደራዊውም ሆነ አመቺ በሆነላቸው መንገድ ራሳቸውን በማጠናከር መቆዬት ግባቸው ነው። ይህ ሁሉ የሚሆነው እነርሱ ባዘጋጁት መንገድ ሲሄድ ለኢትዮጵያ አሳቢ ሊያስመስሉ የሚችሉ አንዳንድ ሥራዎችን ማካሄዳቸው የግድ ነው። ምክንያቱም ይኸውና ለኢትዮጵያ ባያስቡ ኖሮ ነው ይህንን ሁሉ ግንባታ እያካሄዱ ያሉት ብሎ ህዝቡን ለማደናገር ነው። በሌላ መልኩ ግን እነዚህን አውታሮች በዋናነት ለራሳቸው ጥቅም እንዲያመቻቸው ብለው ነው እየገነቧቸው ያሉት። ምክንያቱም የትኛው የረባ ነፃ የሆነ ኢትዮጵያዊ ባለ ሃብት ነው ኢንቨስት አድርጎ የሚታየው? ያለው በትግራይ እንኳ እንደነ ዳዊት ገ/አብሔር ጥናት አድርገው ኃብታቸውን አፍስሰው ለመሥራት ቢመኩሩ በመካልከላቸው በንዴት የተናገሩትን ሰምተናል። እሱ ብቻ አልነበረም ሌሎች ከ20 የበለጡ ባለኃብቶች እንደዚሁ አጥንተው ያቀረቡትን ተነጥቀው ከትግራይ የተባረሩ አሉ። ይሄ በትግራይ ክልል ብቻ የተፈፀመ ሳይሆን በሌላው ክልልም የተፈፀሙ እጅግ ብዙ ናቸው። በስልጣን ያሉት ህወሐት/ኢህአዴጎች ግን በድርጅቶቻቸው ስም ተክለው ባቋቋሚቸው የንግድ ድርጅቶች ማለትም፤ ህወሐት (ትእምት) እግሪ ምትካል ትግራይ ወይም ኢፈርት) በውስጡ ከሰላሳ በላይ ካምፓኒ ሲኖረው፤ ብአዴን ደግሞ ጥረት የሚባለውን በማቋቋም ከአምባሰል ትሬዲንግ ጀምሮ፣ ጥቁር ዓባይ ትራንስፖርት፣ ዳሽን ቢራ፣ ዓባይ ባንክ፣የባሕዳርና የኮምበልቻ ጨርቅጨርቅ ፋብሪካ ከጨረታ ውጪ የራሱ በማድረግ ወዘተ… ሲሆኑ፤ የደቡብ ድርጅትም፣ ወንዶ ትሬዲንግ ግሩፕ የሚባል

ሲያቋቁም፣ ኦህዴድ ደግሞ ዲንሾ በሚል ሥር ልክ እንደ ኢፈርቱ ሰፊ ባይሆንም፣ የቻሉትን ያህል እየሰበሰቡ ራሳቸውንም ሆነ የራሳቸውን አጋሮች እየጠቀሙ መሆኑ ይታወቃል።

ይህንን የመተግበሩ ሂደት ችግር እስካላጋጠመው ድረስ እምቢ ካላችሁ የእንገነጠላለን ካርድን እንደ ማስፈራሪያ በመጠቀም ልክ ለህዝቡ ያዘኑ ይመስል እያደናገሩ ይቀጥሉበታል። እነርሱ ባሉት ይሆናል ወይ የሚለው ራሱ አንድ ነገር ሆኖ፣ ነገር ግን ህዝቡን እያስራቡና ስራ-አጥ እያደረጉት ሲሄዱ፣ በርካታ ወጣት ተስፋ በማጣት የተሻለ ኑሮ ፍለጋ አገሩን ለቆ እየተሰደደ ነው። ለምን እንደዚህ ይደረጋል ብሎ በቁጭት ጥያቄ የሚያቀርበውን አፍነው መኖሪያው እሥር ቤት ነው።

ባጠቃላይ እስከተመቻቸው ድረስ ኢትዮጵያን ይዘው ኃብትዋን በራሳቸው ባገኙት ስልጣን እየሰበሰቡና በነርሱ ዙሪያ ያሉትን ሰዎች እየጠቀሙና እየተጠቀሙ መኖር ሲሆን ዓላማቸው፣ራሳቸው በፈጠሩት ሐፍታም/ብርዢዋ ፣የመድብለ ፓርቲ አሰራር የማይከተል፣የዴሞክራሲና የፍትሕ ሽታ የሌለው አምባገነናዊ ፓርቲ መስርተው ማለቂያ ለሌለው ዘመን ለመግዛት ነው ምኞታቸው። ይህ ካልተሳካ ግን ልክ አቶ ስብሐት ወደ ጥይት እንገባለን እንዳለው አፍርሰውን ለመሄድ ነው ፍላጎታቸው። ዕምነታቸውና አድራሻቸው ግን የት እንደሚሆን አሁን ለመግለፅ ግምት ስለሚሆን ጊዜ ይግለፀው ብየ ባልፈው ይቀለኛል። እኛ ኢትዮጵያዊያን አልታደልንም ያከበርናቸው ያበለፅግናቸው እንዲህ ሲመኙልን ያማል።

ስለዚህ በምር ኢትዮጵያን ለማሳደግና ህዝቦቿን በሠላምና በፍቅር ለማኖር የሚፈልግ መንግሥት ይህንን ሁሉ ተንኮልና ሴራ ማድረግ ይኖርበታል? አይመስለኝም። ምናልባት እኔ ህወሓትን እንደ የትግል መድረክ ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነት መከበርና ለህዝቦቿ እኩልነት ፍትሕ ማምጣት ብዬ አብሬው ስታገል የነበረኝን አረዳድ እና ሁኔታ አሁን በህወሐት ድርጅት አመራር እስከ አሁን በስልጣን ያሉት የሚሠሩትንና የሚናገሩትን ስገነዘብ ኢትዮጵያ ለምንድን ነው ሰው የማይዋጣላት ? የሚል ሐሳብ አዕምሮዬን ይረብሸዋል። በትግል ጊዜ የነበረውንና አሁን ያለውን ለመግለፅ ብሞክርና በዕውነት ባቀርበውም የሚያምኑኝ በጣም ጥቂት እንደሚሆኑ ይገባኛል። ይሁን እንጂ ዕውነት ሁሉ ጊዜ ብትሸፈን እንኳ አትጠፋምና አቀርበው አለሁ።

<u>ህወሓትን እኔ ሳውቀው፤ እና አሁን የደረሰበት ደረጃን ስገመግመው፤</u>

እኔ እስከማውቀው ድረስ ህወሓት እንደ ድርጅት ሲመሰረት የብሄር ጥያቄን እንደ ስልት ተጠቅሞ የትግራይን ህዝብ በብሄር ጥያቄ ካነሳሳና በሥሩ ካደራጀ በኋላ፣ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት፣ እኩልነትንና አንድነትን በማረጋገጥ ፍትሕ የሰፈነባት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መገንባት ነበር የመጨረሻ ግብና ዓላማው።ይህንን ስል በፅሑፍ የሰፈረ ትግራይን የመገንጠል ዓላማ የያዘ ማኒፌስቶ በ1968 ዓ.ም. ጥቅምት ወር ወጥቶ በሐምሌ ወር 1968 ዓ.ም. ከ6 ወራት በኋላ ተቀዶ የተወረወረ ማኒፌስቶ ነበር። ይህ ማኒፌስቶ ብዙ ኢትዮጵያዊያን አንብበውታል፣ ፅፈውበታልም። የትግራይ ህዝብና ሰራዊቱ ከኢትዮጵያዊነት ውጪ ሌላ ሕይወትና ዓላማ ስላልነበረው አልተቀበለውም፣ እንዲማረውና ታጥቆ እንዲታገልለት አልተደረገም። ይህ ሲባልም ይህ ማኒፌስቶ አፅፈው ያመጡት ሰዎች እነ ስብሐት፣ መለስ፣ ስዩም፣ አባይና ሌሎቹም በዚያን ጊዜ ተቀባይ ቢያጡም አዲስ አበባ እስኪ ገቡ ድረስ ሲያመች ብቅ

ሳያመች ጥልቅ እያሉ ውስጥ ውስጡን እየሠሩ መምጣታቸውን አሁን ያለው ሁኔታ ያረጋግጣል የሆነ ሆኖ ህዝቡን ወደ ትግል የማነሳሳትና የማታገል ሥራ በቆራጥ የህወሐት ሰራዊት ኢትዮጵያዊያን መስዋዕትነት እየታጀበ መራራ ትግሉ ቀጠለ። ትግራይን ከፋሽስታዊው የደርግ ሥርዓት ነፃ የማውጣት የትግል ስልቱ የተካሄደው፣ ኢትዮጵያዊ ስሜትና ራዕይ ባልተለየው ሁኔታ ነበር የተካሄደው። ይህንን እውነታ ከሠራዊቱ ጋር ሆነው የታገሉት ሌሎች ኢትዮጵያዊያንና ሰፊው የትግራይ ህዝብ የሚመሰክሩት ሐቅ ነው። ከህወሓት ጎን ተሰልፈው የታገሉት የአማራ ወጣቶች፣ ከደደቢት ጀምሮ እነሚካኤል (አብተው ታከለ ሰሜን ጎንደር) በየካቲት 11, 1967 ዓ.ም. ወንድወሰን ከጎጃም ከ1968 ዓ.ም. ጀምሮ ባህ አበሎም ከወላይታ፣ ከኦሮሞ አበበ የተባሉት ኢትዮጵዊያን በድርጅቱ የሃላፊነትን ቦታ ይዘው የታገሉና ያታገሉ ሰዎችና እንዲሁም አቶ ገሰሰው አየለ የአምስት ዓመት የኢትዮጵያ አርበኛና በደርግ መንግሥት ጊዜ የሽሬ አውራጃ ህዝብ የፓርላማ ተወካይ ጭምር የያዘ ድርጅት ነበር ። በመቀጠል ከኤርትራ ከጎንደር ከወሎ ለትግሉ ቅርብ ከሆኑ አካባቢ ሳያቋርጡ በመከታተል ሴቶችና ወንዶች ወጣት ኢትዮጵያዊያን እየመጡ ድርጅቱን በመቀላቀል በብሔር ጥያቄ ውስጥ ገብተው እስከ ድል ድረስ የታገሉለት ድርጅት እንደነበረ ታሪክ ይመሰክራል።

ህወሓት በትግል ጉዞው የትግራይን ህዝብ ለብቻው በብሄራዊ ትግል ለማነሳሳት ስልቱ ቢጠቀምም፣ ስትራተጂ ዓላማው ኢትዮጵያዊ ስለነበረ ቀደም ብዬ እንደገለፅኩት ከተለያየ ቦታ ለትግል የመጡና ከፋሽሽት የደርግ ስርዓት እያፈነገጡ የሚመጡ፣ በምርኮ የተያዙና በኋላም እንደነ ኢህዴን የመሰሉ ተደራጅተው የራሳችውን ኢትዮጵያዊ ድርጅት ይዘው ለመታገል የመጡ ሁሉ የተከበበ ድርጅት ነበር። በጠቅላላ ድርጅቱ በስትራተጂ ዓላማው የኢትዮጵያ ልዓላዊነትን፣ አንድነትና እኩልነት ማረጋገጥ ስለነበረ ሁኔታውም (atmosphere) ኢትዮጵያዊ ስሜት ያልተለየው ትግል ስለነበረ፣ ከትግራይ ውጪ የሆኑ ሌላ ቋንቋ የሚናገሩ ኢትዮጵያዊያንን የሚያሳትፍ ማዕቀፍ ነበረው። ይሁን እንጂ ህብረተሰቡ ኋላ ቀርነት ያጠቃው ስለሆነ ቀደም ብየ እንደገለፅኩትም ጭምር ሌሎች ችግሮች ስለነበሩ ጠባብነት አይታይም ነበር ማለት እንዳልሆነ ይታወቅልኝ።

በህወሐት ውስጥ የውጪ ተላላኪዎች፣ የሻዕብያ ደቀ መዝሙሮችና ሰርጎ ገቦች እውስጡ ሰርገው በመግባት በድርጅቱ ውስጥ ተሰውረው ይንቀሳቀሱ ጀመር። ህዝቡና ታጋዩ ግን ስልቱና ስትራተጂ ቀና ዓላማውን ጨብጦ ከባድና መራራ ትግል ቢያካሂድም ስልቱ፣ ስትራተጂ ዓላማውን ጠብቆ እንዳይቀጥል አንዴ ብልጭ ሌላ ጊዜ ድርግም እያሉ በስውር የድርጅቱን ቀና ዓላማ የሚበርዙና የሚያሴሩ፣ ይህንንም ለማሳካት የሚታገሉ የውስጥ ጠላቶች ነበሩ።እነዚህ ቀስ በቀስ ዋና የአመራሩን ቦታ በተለያዩ ዘዴዎች እንዴት ለመቆጣጠር እንደ ቻሉ ለመግለፅ በጣም ሰፊ ታሪክ ስለአለው አሁን ለመግለፅ አስቸጋሪ ይመስለኛል። ባዊሩ ፀረ ኢትዮጵያ ተልዕኮ ያላቸው ሰርጎ ገቦች ድርጅቱን በመቆጣጠር፣ ስትራተጂ ዓላማውን በማሽመድመድ፣ በኢትዮጵያ ጥፋትና ኪሳራ እንዲቋጭ ማድረጋቸው ከውጤቱ መገንዘብ ይቻላል። አሁን በስልጣን ያሉት የህወሐት መሪዎች እየተናገሩት ያሉት በትግል ጊዜ በግልፅ ቢናገሩት ኖሮ ታሪኩ ሌላ ይሆን ነበር። ታድያ ምን ዋጋ አለው የነበረውና አሁን የሚባለው የተለዩ እንደነበሩ ለማስረዳት በጣም ከባድ የሆነበት ጊዜ ነውና ለማመን ያስቸግራል።እዚህ ላይ የኢህዴን ወንድሞቻችን የህወሐት ድርጅት ስትራተጂ ዓላማውን እንዳይለቅ የብኩላቸው ጥረት አድርገዋል፣ አወንታዊ ውጤት ባይኖረውም። የሆነ ሆኖ አሁን በሚታየውና በሚነገረው

መፍረድ ኢትዮጵያን ለማዳን የተከፈለ ሁሉ ዋጋ ማሳጣት እንዳይሆን ሰከን ብለን ታሪኩን ማጤን ተገቢ ይመስለኛል። አንድ ቀን ሐቁ ግልፅ የሚሆንበት ጊዜ ይኖራል ብዬ አምናለሁ። ይህ ታሪክ ለትግራይ ህዝብ ያንን ያህል መራራ ትግል አካሂዶ የተገኘው ውጤት፣ የውስጥ እግር እሳትና የማይድን ቁስል ሆኖበት ይገኛል። ኢትዮጵያዊው የህወሓት ሠራዊት በውስጥም ሆነ በውጪ የሚያጋጥሙትን ችግሮች በፅናት እየተዋጋ ትግሉን በማፋፋም ወደ ፊት መገስገሱን ቀጠለ፤ ድርጅቱም በትግራይ ውስጥና ከዚያም ውጪ በሚገኘው የኢትዮጵያ ህዝብ ድጋፍ አግኝቶ በሰው ኃይልና በትጥቅ አቅምም ከሻዕብያ በልጦ ተገኘ። የወታደራዊው ደርግ መንግሥት ሰራዊትም ተዳክሞ ከአጥቂነት ወደ መከላከል ደረጃ ሊወርድ የግድ ሆነ።

በዚህም መሠረት፤ ህወሓት በ፲፱፸፱ ዓ.ም. ደርግን አሸንፎ አዲስ አበባን በሦስትና አራት ዓመታት ውስጥ እንደሚቆጣጠር አልሞ ዕቅድ አወጣ። በዚህም ዓመት 6000 የሚሆኑ የህወሓት ታጋዮችን የአማርኛ ኢንስቲትዩት 'ዛሬማ' በሚባለው የወልቃይት ቦታ አቋቁሞ ያስተምር ጀመር። ከዚያም ቀጥሎ በትግርኛ፣ አማርኛ እና ኦሮምኛ ቋንቋዎች የሚተላለፍ በሰሜን ተራራ አካባቢ ራድዮ ጣቢያ አቋቁሞ ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ በፋሽስታዊው የደርግ መንግሥት ላይ ተቃውሞ እንዲያነሳ፣ ባገዛዙ ላይ እምቢ ብሎ እንዲያምጽ የፕሮፖጋንዳ ስርጭቱን አጧጧፈው። ከትግራይ ክልል ውጪ የሚገኘው ህዝብም የነበረው አገዛዝ በሚያደርገው አፈናና ግድያ የተማረረ ስለነበር ከአገዛዙ እየሸሸ ተቃዋሚዎች ጎን መሰለፉን ቀጠለ።

ባጭሩ ታሪኩ ለማሳጠር በዚህ ሰዓት የጉዞው ታሪክና የትግሉ ሁኔታ እየተቀየረ መጣ። የህወሓት የብሄር ትግል ስልት ትርጉም እያጣ መምጣቱ ግልፅ ሆኖ የትግራይ ህዝብ ትግል ብሎ መቀስቀስ አከተመ። ትግራይ ብሎ ወደ ትግል የማነሳሳቱ ስልት በዚህ ጊዜ ሥራውን አገባድዶ ተጠናቋል። የትግራይ ህዝብን ካጥናፍ እስካጥናፍ ማሰለፍ ስለተቻለ፣ ወቅቱ ጠቅላላ ኢትዮጵያዊያንን በኅብረት ለአንዲት ሉዓላዊነቷ የተጠበቀ፣ ህዝቦቿ በእኩልነትና በፍትሕ የሚተዳደሩባት ኢትዮጵያ የማሰለፍ ጊዜው የሚፈቅደው የትግል ስትራተጂ መሆኑ ግልጽና የማያሻማ ነበር። ቀድሞውም የትግራይ ነጻነት ተብሎ መቀስቀስ ያስፈለገው እኮ፣ ህዝብን ከጎኑ ለማሰለፍ እንጅ ሌላ ፀረ ኢትዮጵያ ተልዕኮ ስላልነበረው፣ የህወሐት ድርጅት ባካሔደው የስልት ትግል የትግራይን ህዝብ አሰልፎ የፋሽሽት ደርግ ከትግራይ ጠራርጎ በማስወጣት ድል መቀዳጀቱ ታሪካዊ ነው። እርግጥ ነው ኢትዮጵያዊያን አልታደልንም ጦርነቱ በኢትዮጵያዊያን መካከል የተካሄደ መራራ ትግል ነበር። ምክንያቱም ቁጭ ብለን ልዩነታችንን በውይይት መፍታት ስላልቻልን ወደ ጦርነት ገባን። ወደድንም ጠላንም ታሪካችን የዕርስ በርስ ውግያ ነው። አሁንም ከዚያ ክብ ቀለበት አልወጣንም። የሆነ ሆኖ ፋሽሽታዊውን ወታደራዊ መንግስት ከትግራይ ከዚያም ከመላው ኢትዮጵያ ግዛት ለማስወገድ የፈሰሰው ኢትዮጵያዊ ደም የትግራይ ህዝብ ይቅርና መላው የኢትዮጵያ ህዝብ እንደሚያከብረው አምናለሁ ።

ይሁን እንጂ የትግራይ ህዝብ ነፃ አውጪ ድርጅት ማለት (ህወሐት) ወይም (TPLF) የሚለውን ስም ያኔ ውኑ ከትግራይ ሳይወጣ ከስልት ትግሉ ድል በኋላ ማክተም ነበረበት ።

የህወሓት መሪዎች የትግራይን ህዝብና ጠቅላላ የኢትዮጵያ ህዝብ በግልፅ የከዱት ከስልቱ ትግል ድል በኋላ ነበር።ክህደቱ የትግራይን ህዝብ የሚያሳዝን ፖለቲካዊም ታሪካዊም ኪሳራ ነበር ። ( The turning point) ስትራተጂ ዓላማችን ልዓላዊነት፣ አንድነትና እኩልነት የሰፈነባት ኢትዮጵያ ነው የምንገነባው ብለው ለትግራይ ህዝብ የገቡትን ቃል ትተው ሸሹት ወይም ከዱት። በዚህ ሰዓት ነበር ህወሓት በጉባኤ ውሳኔ መክሰም አለበት ተብሎ፣ ካሁን በኋላ የትግራይ ነጻ አውጪ ድርጅት ብሎ ትግል የለም፣ ግቡን አሳክቶና መትቶ አጠናቋል መባል የነበረበት ። ቀጣይ ትግላችን የኢትዮጵያ አንድነት፣ ልዓላዊነትና እኩልነት ለማረጋገጥ ብቻ ይሆናል ተብሎ መታወጅም ነበረበት። በስትራተጂ ዓላማቸው መገዛት ነበረባቸው፣ የህወሐት መሪዎች ግን ሠራዊቱንና ህዝቡን አታለሉት፣ ከዱት፣ የትግራይ ህዝብ በልጆቹ የተከዳ ህዝብ ሆነ። <u>የህወሐትን የትግል ስልት ስትራተጂ አድርገው ቀጠሉ፣</u> የትግራይን ኃይል ለኢትዮጵያ ጥፋት አሰለፉት። ኢትዮጵያዊነቱን ለጥቅማቸውና ለስልጣናቸው መጠበቂያ ሸጡት።የህወሐት ድርጅት እንደ ድርጅት የፈፀመው ስልታዊ ታሪክ ታቅቦ ለዘመናት እየተዘከረ እንዲኖር፣ የኢትዮጵያ ህዝብም የትግራይ  ህዝብ ውለታ በማሰብ ፣ትግል ወደ ተካሄደባቸው የትግራይ ተራራዎች በመጓዝ እየጎበኙ፣ እንዲያውቀው፣ ማድረግ ሲገባ፣ህወሓትን እንደ ድርጅት፣ ያላንዳች ዓላማ ወይም ለሌላ ሥውር ዓላማቸው፣ተሸክመውት፣አዲስ አበባ ቤተ መንግሥት ይዘውት ገቡ። ለኢትዮጵያ ጥቅም ሳይቆሙ ለሻዕቢያው ኤርትራ ጠበቃ ሁነው ተገኙ። በትግራይ መሬት ያለ ፍርድ እየረሸኑ፣ ሰላይ፣ የህወሐት ጠላት እየተባለ፣ በጅምላ የቀበሩት እያለ፣ አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ የደርግ መንግሥት እየረሸነ በጅምላ የቀበራቸውን ከጉድጓድ እያወጡ ህዝብ እያለቀሰ በቃን እስኪል ድረስ አሳዩት። ጅብ በማያውቁት አገር ሔዶ አጎዛ አንጥፉልኝ አለ እንደሚባለው ሆነ። በነሱ ቤት የደርግን ጭካኔ ለማጋለጥ መሆኑ ነው፣ ህዝብ አወቁሽ ናቁሽ እንደሚላቸው ይገነዘቡ ይሆን? አገር ወዳድ ሆኑና አገር እየበተኑ ኢትዮጵያ አንድ አደረግናት፣ አሉ፣ እኛ ባንኖር ኑሮ ኢትዮጵያ ተበትና ትቀር ነበር አሉ፣አሁን ደግሞ ትበተናለች እያሉን ነው ምንስ ያላሉት አለ፤ ሐቁ ግን ሊላ ነው። ኢትዮጵያን አንድ የሚያደርግ ፓርቲ መመስረት ሲገባቸው ኢህአዴግ የሚል ግንባር ፈጠሩ። አቶ ስብሐት ነጋ እና ተከታዮቹ  በግልፅ የትግራይን ህዝብንና በጠቅላላ የኢትዮጵያን ህዝብ ከዱ። አሁን አቶ ስብሐት ነጋ ኢህኣዴግ መጥፋት አለበት፣ ራሱን ማጥፋት አለበት፣ ራሱንም እንደሚያጠፋ ያውቃል እያለ የሚለፈልፈው፣ የህወሓት መሪዎች አዲስ አበባ ከመግባታቸው በፊት በህውሐት ድርጅት ላይ መፈፀም የነበረበት ተግባር ነበር። ልክ ነው ዛሬ የቡርዥዋ ፓርቲ ለመመስረት ከተፈለገ ኢህአዴግ ድርጅት መክሰም/መጥፋት አለበት። ድርጅት አንድ ዓላማ ለማስፈፀም የሚፈጠር መሳሪያ ነው። ከተጠቀምክበት በኋላ በሌላ ይቀየራል። እነ ስብሐት ነጋ በዚህ ብቻ አላቆሙም ህወሐት ራሱ ወደ ኢህዴን ድርጅት መቀየር ሲገባው የኢትዮጵያ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (EPDM) ከኢትዮጵያዊነት ንቅናቄው ዝቅ አድርገው ብአዴን ወደተባለ የአማራ ብሔር ብቻ ተወካይ እንዲሆን አሽመደመዱት። የአማራ ዘር እንጂ ከኢትዮጵያዊነት ውጪ የአማራ ማንነት የሚባል የለም ብሎ የሚያምነውን ኢትዮጵያዊ አማራን ሊያሽምደምዱት፣ ኢትዮጵያዊ ማንነቱን ሊነጥቁትና ሊቀይሩት ከብአዴን ጋር በመተባበር ከፍተኛ ግፍ እንዲፈፀምበት ተደርጓል። አሁንም ድርጊቱ በከፋ መልኩ እየቀጠለ ይገኛል።በጣም የሚያሳዝነው የነዚህ ሁለቱ ተንኮል ግፍ ቀማሽ የአማራ ህዝብና የትግራይ ህዝብ መሆኑ ነው ፣ ይህንን የህወሐት ከፋፍለህ ግዛ ተንኮል ሲጀመር የኢህዴን አባሎች እሺ ብለው ያልተቀበሉ ሕይወት ከፍለውበታል ገና ታሪኩ

ለወደፊቱ ይወጣል። ለምሳሌ ከተቃወሙት እነ አቶ ያሬድ ጥበቡ ጄኔራል ሃይሌ ጥላሁን፣ አቶ ተፈራ ዋልዋ ወዘተ የተረሸኑ እነ ሐውጃን እና ሙሉዓለም አበበ እና ሌሎችም ።

ከህወሐት መሪዎች ጋር በመተባበር ድርጊቱን የፈፀሙና ያስፈፀሙ ከብዙዎቹ በጥቂቱ አቶ ታምራት ያይኔ፣ አቶ በረከት ስምዖን፣ አቶ ታደሰ ካሳ (ጥንቅሽ)፣ አቶ ህላዌ ዮሴፍ፣ አቶ አዲሱ ለገሰ፣ አቶ ኩማ ዴሜቅሳ፣ አቶ አባዱላ ገምዳ፣ አቶ መለስ የተባሉ የወሎ ዞን አስተዳዳሪ የነበሩትን መጥቀስ ይቻላል።

የህወሐት ሰራዊት በትግራይ ውስጥ የነበረው የጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ሰራዊት በማሸነፍ ከትግራይ መሬት ጠራርጎ ነፃ አወጣ። ከዚያ በኋላ የሚቀጥለው ጉዞ የጊዜያዊ ወታደራዊ ፋሽሽት መንግሥት ከመላው የኢትዮጵያ ግዛት ማስወግድ ቀጣይ ስትራተጂ ዓላማው እንደነበር ግልፅ ነው። የህወሐት ድርጅት ሰራዊት ለቀጣይ ዘመቻ ትዕዛዝ ሲጠብቅ ወደ ማህል ኢትዮጵያ ለመዝመት ስሙን ሳይቀይር ስልቱንና ስትራተጂውን ሳይወያይበትና ዝግጅት ሳያደርግ በህወሐት መሪዎች ትዕዛዝ ወደ ማህል ኢትዮጵያ ክተት ሲሉት እምቢ አለ። ከ30 እስከ 40ሺ የሚገመት የህወሐት ሰራዊት የተሰጠውን ቦታ እየተወ መቀሌ ላይ ተሰባሰበ። ለአመራሮች ድንጋጤ የፈጠረ እንቅስቃሴ ነበር የሰራዊቱ ጥያቄ፦ ለምን? በምን ዓላማ ብቻየን ዕዋጋለሁ ሁሉ ኢትዮጵያዊ ይምጣና አብረን እንሰለፍ ላንድነት ባንድነት ተራምደን እኩል መስዋዕት ከፍለን አዲስ አበባ መግባት አለብን የሚል ነበር። ትግሉን ኢትዮጵያዊ ከማድረግም በኩል ስትራተጂካዊ ተልዕኮ ነበረው፣ ከሰራዊት አስተዋፅኦም በኩልም ሲታይ ጥያቄው ትክክል ነበር። የህወሐት አመራር ጥያቄውን ሳይቀበል ቀረ፣ እነ መለስ ዜናዊ ስልጣን ለመያዝና አዲስ አበባ ለመግባት ተቻኮሉ። የተደበቀ ዓላማ ስለነበራቸው ኢትዮጵያን ለማዳን፣ አንድነትዋንና ልዓላዊነትዋ ለማረጋገጥ ሳይሆን የጠላቶቻችን ተልዕኮ ለማስፈፀም ነበር ሩጫው። በዚያን ጊዜ ከነበሩት የጦር መሪዎች ሜጀር ጀኔራል ፃድቃን ስለዚህ ጉዳይ ባዲስ ዘመን ጋዜጣ "የህወሐት ሰራዊት ጠባብነት ስላጠቃው ትግራይን ነፃ ካወጣ በኋላ ከዚያ ውጭ ለመዋጋት አልፈለገም" ማለታቸው ይታወሳል። የህወሐት ስራዊት በጠባብነት ተወቀሰ፣ ተወንጀለ። እንግዲህ ያብየ ለምየ መሆኑ ነው፣ ፍርዱን ላንባቢ እተወው አለሁ። በመቀጠል ዕንቅፋት ያኗቸውንና ኢትዮጵያዊ ስሜት ያላቸውን ሁሉ እየጠረጉ አዲስ አበባ ገቡ። ከዚያ በኋላ የሆነውን ያዲስ አበባ ከተማ ህዝብ የሚያውቀው ስለሆነ አልገፋበትም።

የህወሐት ስራዊት አሁንም ትግሉን አላቋረጠም፣ አዲስ አበባ እንደገቡ በ1985 ዓ.ም. በተነሳው እንቅስቃሴ፣ የቀረቡት ጥያቄዎች እንዲህ የሚሉ ነበሩ፦ ለምን የኤርትራን ጉዳይ ለማስፈፀም ይሮጣል? የኤርትራ አዋሳኝ ከየት እስከ የት ነው? የባህር በር ጉዳይ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር እንወያይበት? ሕጋዊ ያልሆነ ለኤርትራ ዕውቅያ ለምን እንሰጣለን? ኤርትራ ለማስገንጠል የህወሐት ካድሬ ለምን ይዘምታል? ለምን የቀድሞ መንግሥት ሠራዊት ይበተናል? ለምን ስልጠና ተስጥቶት አይጠናከርም? ሰራዊታችን አንበትን ? ሻዕብያ ሊወረን ነው? የሻዕብያ ሰራዊት ማቋቋሚያ አንድ ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር ለምን ተሰጠ? ኢህአዴግ የሲብል ሠራተኛ ኢትዮጵያዊያን ቦታ ለምን ይወስዳል? ሠራተኛው መበተን የለበትም ወንጀል ካለው በሕግ ይታይ? ለምን ወደ ሶፋ ጉተታ ገባን? ወዘተ የሚሉ ኢትዮጵያዊ ጥያቄ ቀርበው ነበር። ፀረ ኢትዮጵያ አቋም የያዙት የህወሐት መሪዎች የታጋዮቹ ጥያቄ በስነ ስርዓት መመለስ ሲገባቸው፣ ከፍተኛ

እስርና ማንገላታት በመፈፀም 32ሺ የሚሆኑ የሠራዊቱ ታጋዮች በህወሐት መሪዎች ስልጣን እንደ ተጋፉ ተቆጥረው አድመኞች ተብለው ከሕግ ውጪ ያለፍርድ 32ሺ የትግራይ ህዝብ ልጆች ታጋይ ሰራዊት? ትጥቁን አስፈትተው እነ አቶ መለስ ዜናዊ ለኢትዮጵያ ልዕልነትና አንድነት እየተዋጋ የመጣው ስራዊት ቆሻሻዎች ጉድፎች ናቸው በማለት እንዲበተኑ ተደረጉ፣ እየተሰቃዩ ተደበድበው የታሰሩ የተገደሉም ነበሩ። በሆለታ እስር ቤት ብቻ 4000 የሚያህሉ ታስረው ተሰቃይተዋል።የህወሐት አባሎች በአዲስ አበባ ከተማ ግፍ እየደረሰባቸው ምን አደረጉ ብሎ ከነሱ ጋር የቆመ ኢትዮጵያዊ አልነበረም። እንዲታወቅም ሊያደርግ የሚችል ሐይል አልነበረም። በዚያን ጊዜ ህወሐት ብሎ ነፃ አውጪ ባአዲስ አበባ ለምን? የሚለው ጥያቄ እንኳን ለከተማ ህዝብ ለአቶ መለስ ዜናዊና ለተከታዮቻቸው እንጂ ለህወሐት ድርጅት ራሱ ግልፅ የነበረ አይመስለኝም። የሰራዊት ማመጣጠንም ምክንያት አድርገው ብዙ አባረሩ። እዚህ ላይ ሠራዊቱ መቀነስ የለበትም ማለቴ ሳይሆን፣ለሻዕብያ ሰራዊት ማጠናከሪያ ካንድ ቢሊዮን በላይ ወጪ ሲያደርግ፣ ዕድሜ ልኩን በድርጅቱ ውስጥ ላደገ ሰው፣ ድንገተኛና ቀደም ተብሎም እየተለማመደው ያልመጣ፣ ኑሮዬ ድርጅቴ ብሎ ለመጣ የሠራዊት አባል፣ ምንም ዓይነት መቋቋሚያ ሳታዘጋጅለት እንደ ድንገተኛ ደራሽ ውሃ ጠራርጎ ሲያባርር የደርግ ሰራዊትም እንዲሁ ማባረር አግባብነት የለውም ማለት ብቻ ሳይሆን፣ድርጊቱ ፀረ ኢትዮጵያ የሆነና ከክህደት በላይ መስሎ ይሰማኛል። በጥሩ ስምም እኮ ማሰናበት ያባት ነው፤ አብዛኞቹን የተለያዩ ስሞች እየለጠፉ እኮ ነው ያባረሯቸው። በየሄዱበት የትውልድ ስፍራቸውም ደብዳቤ ይዘው እንዲሄዱና ባይነ-ቁራኛ እንዲታዩ ለሚመለከታቸው ክፍሎች ሳይቀር ተነግሯቸው ነበር።

ይህንን ችግር ለመቅረፍ የትግራይ ህዝብና ልጆቹ ከፍተኛ መራራ ትግል አካሂደዋል። ትግሉ ለትግራይ ህዝብ ድርብ ድርብርብ ነበር። የውስጥም የውጪም ጠላት ማለት ነው። አሁንም ትግሉ ቀጥሏል። የትግራይ ህዝብ የህወሐት ድርጅትን መቃወም የጀመረው ገና የድርጅቱ ስህተት መታየት ሲጀምር ነበር። በ1975 ዓ.ም. አካባቢ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ነፃነት የሚል ድርጅት በዶ/ር ሐይሌ የሚመራ (አሁን በሕይወት የሉም) በሱዳን ስደት የሚገኘው የትግራይ ህዝብ በመመስረት ሲታገል መቆየቱ ይታወሳል። የህወሐት ድርጅት አዲስ አበባ እንደገባ ባንሳው ጥያቄና ትግል፣ እንዲሁም በኢትዮጵያ የሰራዊት አስተዋፅኦ ቅነሳ ምክንያት በማድረግ በቂም በቀል ሰራዊቱ ለመበተን በጠቅላላ ከ65ሺ በላይ ስራዊት እንደተባረረ ይታወቃል፣ ይህ ብሶት የወለደው ሐይል ራሱ በመሰባሰብ እንደገና ወደ ትጥቅ ትግል በመግባት (ድምሒት) ዲሞክራሲያዊ ምንቅስቃስ ህዝብ ትግራይ (TPDM) የሚል ድርጅት በማቋቋም በትግራይ መረብና ተከዜ ኤርትራ አከባቢ የትጥቅ ትግል በማካሔድ ላይ ይገኛል። በ1987 ዓ.ም. የህወሐት ድርጅት ከመሰረቱትና ለረጅም ጊዜ በድርጅቱ ውስጥ የታገሉ ቄምር ያሉበት በአመሪካና በአውሮፓ በስደት የሚገኙ የትግራይ ተወላጆች ያቋቋሙት (ዴ.ም.ት.) ዴምክራሲያዊ ምትህብባር ትግራይ (TAND) Tgray Allians For National Demcoracy የሚባል ድርጅት በማቋቋም በትግል ላይ እንዳሉ የታወቀ ነው። በትግራይ ውስጥም ዓረና ትግራይ ለዲሞክራሲና ለልዓላዊነት የሚል ድርጅት በማቋቋም በምርጫ ተወዳድሮ ለማሸነፍ የሚታገል የክልል ፓርቲ መስርቶ ብዙ መስዋዕትና ግፍ እየደረሰበት የሚገኝ የትግራይ ህዝብ ድርጅት እንዳለ በፖለቲካ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ያውቃሉ።የትግራይ ህዝብ አልታገለም/አይታገልም ያለ ለሚሉ ሁሉ ከዚህ የበለጠ መልስ አይኖረኝም። የትግራይ ህዝብ ያደረገውን ትግል ጠቅላላ

የኢትዮጵያ ህዝብ የሚረዳበት ጊዜ ቀርቧል የሚል እምነት አለኝ። የትግራይ ህዝብን በጅምላ የችግሩ አካል አድርጎ የሚመለከት አልታጣም ለትግራይ ህዝብ በነ መለስ ዜናዊ ስብሐት ነጋ እና በጠቅላላ በህወሐ/ኢህዴግ ድርጊት ዓይን የትግራይን ህዝብና ልጆቹ የሚወነጅል በጠላት ዓይን የሚመለከት ኢትዮጵዊ ቁጥሩ ቀላል ላይሆን ይችላል ያሳዝንናል ይህ ዓይነት አመለካከት የሚጠቅመው ለገዢው ፓርቲ ሲሆን ለተቃዋሚዎች ግን በስልትም በስተራተጂም የሚጎዳ አስተሳሰብ ስለሆነ ሐቁን ጨብጦ መጓዝ ያስፈልጋል ለዚህ ሁሉ ስህተት መንስኤው፣የትግራይ ህዝብ ያካሄደው ትግልና አሁን እያካሔደው ያለ ትግል አለመገንዘብና ለምን ዓላማ እንደነበረ በጥልቅ ካለመረዳት መሆኑ ግልፅ ነው። በሥልጣን ያሉት መሪዎችም እነርሱን በመፃረር የተካሄደው ኢትዮጵያዊ ትግል እንዲታወቅ ፍላጎትም፣ ሞራልም አልነበራቸውም የላቸውምም።

አሁን ግን የትግራይ ህዝብ ብቻውን አይደለምና ጠቅላላው የኢትዮጵያ ህዝብ ከርሱ ጋር ነው ያለው ስለዚህ የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር የትግራይ ህዝብ እንደ ልማዱ ሆ ብሎ መነሳቱን አልጠራጠርም ለኢትዮጵያ አገሩ እንደ አባቶቹ ደሙን ያፈሳል፣ አጥንቱን ይከሰክሳል፣ አሁን ያለው ፀረ ኢትዮጵያ ዓላማ በመቀልበስ ዳግም ታሪክን ይሠራል፤ የኢትዮጵያን አንድነት፣ እኩልነትንና ልአላዊነትን ያረጋግጣል።

ምዕራባዉያን ጠላቶቻችንና የኢሳያስ ደቀ-መዛሙርት፣ በህወሓት-ኢህአዴግ ትግል ውስጥ ኢትዮጵያ አገራችንን የሚበታትንና የሚያዳክም ዓላማ አስርገው በማስገባት አመራሩን ተቆጣጥረው፣ ተቀባይ አፍርተው፣ ዓላማቸውን አንድ በአንድ እንዲፈፀም አደረጉ። ኢትዮጵያ እንደ ዋዛ በጠላቶቻችን ቁጥጥር ስር ገባች፣ ኃይልዋ ተበተነ፣ ልጆቿ በክልል ተለያዩ፣ አንድነት፣ መመካከርና መደማመጥ ጠፋ፣ ተበታትኖ ማልቀስ ማለት ይልኋል ይህ ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ ላንዴ ሰከን በልና ጠላትህና ወዳጅህ በመለየት ያገር አድን ጉዞህን ጀምር ።

አንዳንድ ኢትዮጵያዊያን ወገኖች ኢትዮጵያ አትጠፋም፣ አትበተንም፣ ኢትዮጵያ እግዚአብሔር ከርሷ ጋር ነው፣ የሚሉ አሉ ሊሆንም ይችላል። ይሁን እንጂ አንድ አገር ህልውናው የሚጠፋው የህዝቡ አስተሳሰብ ሲለወጥ፣ አገራዊ ማንነቱ፣ ባህሉ፣ ስሜቱና ታሪኩ ሲለወጥ መሰለኝ። ይህንን ደግሞ በተግባር እያየነው ያለና የሚያስፈራው ገጽታችን ነው።

ያለው አገዛዝ ወጣቱን ኢትዮጵያዊ ስሜትና የሃገር ፍቅር ኖሮት እንዲያድግ አይደለም እየቀረፀው ያለው። ይልቁንስ ደንታ ቢስ፣ ለራሱ ብቻ የሚያስብ፣ በጫትና ሌሎች ሱሶች ሲጠመድ፣ አንድ መንግሥት እንደ ኃላፊነት የሚሰማው መጠንና እንዴት ወላጆቻችን በመልካም ስነ-ምግባር ኮትኩተው እንዳሳደጉን እየታወቀ፣ ስላገሩ የሚያስብ ትውልድን ሆነ ተብሎ ተመናምኖ እንዲጠፋ እየተደረገ እንዳለ፣ ሁላችንም በውል ልንገነዘነው የሚገባን ይመስለኛል። ወጣቱ ስላገሩ ሳይሆን ስለ ዕለት ተዕለት ኑሮው ብቻው እንዲያስብ፣ ዝርፊያና ሙስና የወቅቱ መገለጫ በመሆኑም ስርቆት እና ብልግና አሳፋሪ መሆናቸው ቀርቶ የአዋቂነትና የብልጥነት መለኪያ እየሆነ መጥቷል። ባጠቃላይ ሆነ ተብሎ ስለ ሃገሩ የሚያስብና የሚቆረቆር ተቋምና የኅብረተሰብ ክፍልን ማሽማቀቅና በሂደትም ተስፋ ቆርጦ ሽብረክ እንዲልና እጉልበታቸው ሥር ወድቆ ፍርፋሪ ለቃሚ ማድረግ፣ ካልሆነም አገሩን ለቆ መሰደድ ዕጣው እንዲሆን በሚገባ

እየተሠራበት ያለው ሁኔታ ነው። ይህንን በፅናት ተቃውመው የሚታገሉትን፣ በተለያየ መንገድ ወጣቱን ለማስተማር ጥረት ከሚያደርጉት ተቋሞች አንዷና በፊትም ኢትዮጵያ እንደ ኢትዮጵያ ጸንታ እንድትቀጥል የበኩሏን አስተዋጽዖ ካደረጉት መካከል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን መሆኗ ይታወቃል። ሌሎች እንደ የኢትዮጵያ እስልምና ሐይማኖትም የመሰሉ ተቋሞች ያላቸው አገራዊ ተራ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። አገራችን እንዳትጠፋ የምንሰጋውና የምንፈራው፣ አገር አጥፊ የሆኑት አስተሳሰቦችና ራዕዮች ሲበቅሉና ሲስፋፉ እያየን በመሆናችን ነው ። ስለዚህ ባሁኑ ሰዓት አስቸኳይ የአገር አድን እንቅስቃሴ ያስፈልጋል። ኢትዮጵያ አትጠፋም ማለቱ ብቻ አያዋጣም። ልክ ነው የመሸነፍ ስሜት መኖር የለበትም። የኛ የትግል መርህ፣ ኢትዮጵያን ማዳን፣ ኢትዮጵያ ትኑር የሚል ብቻ መሆን አለበት። ኢትዮጵያዊነት እንዲጠነክርና እንዲስፋፋ የሁሉም ህዝብ በኢትዮጵያ ምድር የበቀሉ ሁሉ ገዢ አስተሳሰብ እንዲሆን መታገል፣ የነበረውን ኢትዮጵያዊነት ለማስመለስና ለማጠናከር ትግሉ መጧጧፍ አለበት።

አንድ አገር፣ አንድ ማንነት፣ አንድ ህዝብ፣ አንድ ሰንደቅ ዓላማ ሶስት ቀለማት፤ አረንጓዴ፣ቢጫና ቀይ ቀለማት ያሏት ሰንደቅ ዓላማ፣ አንድ የሁላችን መግባቢያ ቋንቋ አማርኛ እንደነበረንና እንዳለን ማስረገጥ ተገቢ ነው። ሁሉ ኢትዮጵያዊ ያለ ልዩነት፣ ባንድነት እንዲተምና እንዲታገል ማነሳሳት ትግል፣ ትግል፣ ትግል፣ ማካሄድ ያስፈልጋል። ይህንን አገር አድን መፈክር ለማብጠልጠልና ብሎም ሃፍረት እንዲሰማን የሩቅም ሆነ የቅርብ ጠላቶቻችን በተለያዩ መንገድ ከፍተኛ ትግል አካሂደዋል፣ አሁንም እያካሄዱም ናቸው።

ለምሳሌ አሳፋሪ ሆኖ እያለ በድፍረትና በግልፅ እየተነገረ ያለው አነጋገር፤ እኔ ትግራይ ነኝ፣ እኔ ሶማሌ፣ እኔ አማራ ነኝ ወዘተ… ይልና፤ ኢትዮጵያዊ ልሆን የምችለው፣ መጀመሪያ ትግራዋይ፣ ሶማሌ፣ አማራና ወዘተ… ሆኜ ከተፈጠርኩኝ በኋላ ነው፤ ሲሉ በስፋት ይደመጣሉ። ከአሁን በፊት እንደዚህ ዓይነት አባባል አልነበረም። ይህ አሳፋሪና በታኝ አስተሳሰብ በሁሉም ክልሎች፣ ብሔር ብሔረሰብ እንዲስፋፋ ትግል ተካሂዶበታል፣ አሁንም እየቀጠለ ነው። ይህ አስተሳሰብ ከሁሉ በፊት በኤርትራና በኦሮሞ ቀደም ሲል የተጀመረና የተስፋፋ እንደነበረና ኤርትራን ማጣትም የዚህ ውጤት መሆኑ ለመረዳት የሚቸግር አይመስለኝም ። ይህ አሳፋሪ አስተሳስብ ቀይ ባሕር ተሻግሮ ኤርትራ የገባ በሽታ ቢሆንም አሁን ወደ መሃል አገር በመስፋፋት አድጎ መንግሥታዊ አስተሳሰብ ሁኗል።

በኢትዮጵያ ምድር የበቀሉ ብሔር ብሔረሰብ የበቀሉበት መሬት ላይ አፍርተው እየበሉ እየለበሱ ያደጉበትና ልጆቻችውን ያሳደጉበት፣ የበለፀጉበትና ከውጪ ጠላት እየተከላከሉ እስከዛሬ ያቆዩዋትን አገርና ምድር ረስተው ወይም ክደው፣ እኔ ኢትዮጵያዊ ከመሆኔ በፊት ሌላ ነበርኩኝ ማለት ምን ዓይነት የሚያሳፍር ስህተት እንደሆነ ለማስረዳት ከባድ የሆነበት ጊዜ ደርስናል። እማን ላይ ቁመሽ ማንን ታሚያለሽ የሚባለው አነጋገርን ያስታውሰናል። ዛሬ እኔ ማንነቴ ትግራይ ነኝ፣ ሶማሌ ነኝ፣ ኦሮሞ ነኝ፣ አማራ ነኝ፣ ይባልና ኢትዮጵያዊ መሆንሳ ለምን ስትል ኢትዮጵያዊነቴን ማን ይከለክለኛል? ማን ነው ሰጪ እና ከልካይ? ያደረገው ይሉናል ። ጋምቤላ እኮ ተጠቃ፣ አማራ ታረደ፣ ኦሮሞ ተገደለ፣ ትግራይ ታሰረ ስትል እሱ ማን ነው? እሱማ ከክልል ውጪ ነው። ጋምቤላ፣ የጋምቤላ ጉዳይ ነው፣ ራሱ ተጠናክሮ ራሱን መከላከል አለበት፣ አያገባኝም

የኔን ችግር እኔ ራሴ እወጣዋለሁ፣ ሌላውን ራሱ ያድን ይላል። እሱ እኮ ኢትዮጵያዊ ወንድምህ ነው ስትለው፣ እኔማ ኦሮሞ ነኝ፣ ኢትዮጵያዊ አይደለሁም ይላል፤ ትግራይስ ስትለው እሱማ ወያኔ ነው ወይም ደግሞ እሱ የፌደራል መንግሥቱ ጉዳይ ነው የሚል የሸፍጥ መልስ ታገኛለህ።

ያሳዝናል የአንድነታችን መድከም፣ የመተጋገዝና የመረዳዳት ባህላችን መጥፋት የሚካሄድበት አሳፋሪ ሁኔታ እያየን ነው። አንዱ የትግላችን አገባብ ይህንን አስተሳሰብ ከህዝባችን ለማስወገድ መጣር መሆን ያለበት ይመስለኛል። ለዚህ መድሐኒቱ፣ ያለችን አንዲት አገር እንደሆነች፣ ማንነታችንም አንድ ኢትዮጵያዊነት እንደሆነ፣ በዚች አገርና ምድር ያለው ህዝብ፣ አንድ ህዝብ እንደሆነ እንጂ 'ህዝቦች' የሚለው መጠሪያ የኢትዮጵያ ጠላቶች እኛን ለመከፋፈል ያመጡብን አደገኛ አስተሳሰብ እንደሆነ ማስረገጥ፤ እኛ ኢትዮጵያዊያን እንደሆንን አንድ ህዝብ እንጂ 'ህዝቦች' የሚል መጠሪያ የጠላቶቻችን ቋንቋ ወይም አነጋገር ነው፣ እኛን በክልል ለያይተው አንድነታችን አጥፍተው ህዝቦች ይሉናል፣ የትግራይ መንግሥት፣ የኦሮሞ መንግሥት፣ የአማራ፣ የደቡብ ወዘተ... መንግሥት፣ እያሉ በኢትዮጵያ ምድር ውስጥ ሌሎች አገሮች፣ ህዝቦችና ብሔር ብሔረሰቦች የሚል ስም ሰጥተው እንደ አንድ አገር በጋራ የምንግባባበት ያማርኛ ቋንቋንም እንዲዳከም አደረጉት።

አንድ አገርና አንድ ኢትዮጵያዊነት እያለን፣ የተለያዩ ቋንቋዎቻችንን፣ ታሪካችንን፣ ባህሎቻችንን፣ በእኩልነት እያሳደግን አንድነታችንን አበልፅገን መኖር ስንችል፣ ለምንድነው ተለያይታችሁ ኑሩ የምንባለው? እንዴት አድርጎ ነው አንድ ህዝብ ተለያይተህና ተበታትነህ ማደግ ትችላለህ የሚባለው? ይሄ ዘዴ ከፋፍሎ ለመግዛት ከመጥቀሙ ባሻገር፣ አገራችንን የሚበትንና የሚያዳከም ዓላማ ስላለው የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ አስተውል፣ እየለያዩን ነው ብዬ ማስታወስ እፈልጋለሁ። የህወሓት/ኢህአዴግና ዓላማ፣ እያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ እርስ በርስ እያናከሱና እያባሉ፣ የግዛት ዘመናቸውን ማራዘም አንዱ ግብ ሲሆን፣ ይህም ባይሳካላቸው በስተመጨረሻ ላይ አንድነታችንን አፍርሰውና በታትነው የምዕራባዊያን ጠላቶቻችንንና የኢሳያስ ተልዕኮን ማረጋገጥ ነው።

ስለዚህ ሲበትኑን መሰባሰብ፣ ሲያጣሉን መታረቅ፣ ሲያዳክሙን መበርታትና መጠናከር አለብን። እናስተውል  እነሱ እና እኛ እንድንባባልና መሃላችን ውስጥ ጥርጣሬን በመዝራት መተማመን እንዳይኖር የተደረገው ሴራን ማክሸፍ ይጠበቅብናል። ጨርሰው ሳያጠፉን  እንንቃ እንተባበር፣ ሁሉም የተወሰነ ልዩነቶቹን ወደጎን በማድረግ ይነሳ። ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚል ሁሉ በሚመቸው መንገድ ይደራጅ፣ ይሰባሰብ፣ ኃይሉንና ገንዘቡን፣ ዕውቀቱንና ሕይወቱንም ቄምር ሰጥቶ ወላጆቻችን ያስረከቡንን አገራችንን፣ መሬታችንና የጥንቱ ማንነታችንን ለማጠናከር እንነሳ። ሁላችንም የቤት ሥራችንን ከምር ከሠራን፣ ውጣ ውረድ ሊኖረው ቢችልም እንኳን ሐቅ ይዘን እስከሆንን ድረስ ማሸነፋችን የግድ ይሆናል።

ኢትዮጵያ ለዘልዓለም ትኑር።

ከመኮንን ዘለለው

Maryland, U. S. A